**ዳግማዊ የመላው ዐማራ ሕዝብ ድርጅት (ዳግማዊ መዐሕድ )**

**All Amara People's Organization II (AAPO II)**

E-mail: AAPO2nd@gmail.com
Telephone: +16788494703


## *የፖለቲካ ፕሮግራም*

### *መግቢያ:-*

የአማራ ህዝብ ትግል ህልውናን የማስከበር ትግል ነው፡፡ አማራ እንደ ህዝብ ህልውናው እንዲጠፋ በትግራይ ዘረኛ አምባገነኖች የተፈረደበትና ሰፊ የዘር ማጥፋት ዘመቻ እየተካሄደበት ያለ ነገድ ነው። ስለሆነም አማራ ህልውናው አደጋ ውስጥ ወድቆ ይገኛል፡፡ የአማራ ትግል ህልውናውን የማስቀጠልና ያለማስቀጠል ጉዳይ ነው። አማራን ከምድረ ኢትዮጵያ ካላጠፋን በስተቀረ የትግራይ ሪፑብሊክና የበላይነት ሊረጋገጥ አይችልም የሚሉት የትግራይ ጠባብ ብሔርተኞች፣ አማራን ለማጥፋት በሚል እኩይ አስተሳሰብ ተጠምደው፣ ላለፉት አራት አስርተ-ዓመታት አማራን እንዴት እንደሚያጠፉ በትግል ሰነዳቸው ቀዳሚ አጀንዳ በማድረግ ፕሮግራም ነድፈው በስፋት ሲንቀሳቀሱ ቆይተዋል፡፡ አሁንም በዚሁ የጥፋት ተልኳቸው በመግፋት፣ ከመቸውም ጊዜ በባሰና በከፋ ሁኔታ የአማራውን ዘር ከምድረ ገጽ ለማጥፋት በስፋት እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ፡፡ ለዚህም በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙት ብሔሮች እና ህዝቦች ዘንድ መጠነ ሠፊና መሠረተ ቢስ ፀረ-አማራ ጥላቻ ፕሮፓጋንዳ መንዛት ብቻ ሳይሆን፣ ሽፋን በመስጠት ሌሎች ብሔሮችና ብሔረሰቦች በአማራው ነገድ ላይ በጥላቻና ቂም እንዲነሳሱና እስከፊ የዘር ማጥፋት እርምጃ ድረስ እንዲወስዱ አድርገዋቸዋል።

ከውጭ አገራት፤ በተለይም ከጎረቤት አገራት ጋር በአማራው መሰረታዊ ህልውናና ጥቅም ላይ በማናለብኝነት እንዳሻቸው በመደራደር፣ ርስቱን ብቻ ሳይሆን ህይወቱንም ጭምር ለታሪካዊ የውስጥና የውጭ ጠላቶቹ አሳልፎ በመስጠት እንዲነጠቅ በማድረግ፣ በህልውናው ላይ ሰፊ ወጥመድ አዘጋጅተውበት ይገኛሉ፡፡

አማራው ወደዚህ የእልቂት እና የዘር መጥፋት ክፉ ዘመን ከመሸጋገሩ በፊት በዋነኝነት ለኢትዮጵያ አለኝታ ሆኖ እጅግ መራራ መስዋእት ሲከፍል መቆየቱ በስፋት የሚታወቅ ሀቅ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በዘመናት ታሪኳ፣ ለመላው የዓለም ጭቁን ሕዝብ የነፃነት ዓርማ፣ መመኪያና መከታ ሆና በቆየችባቸው ዘመናት አማራ እንደ ህዝብ ግንባር ቀደም ተሰላፊ ሆኖ ከባድ መስዋእት ሲከፍል ቆይቷል፡፡ ነገር ግን ዛሬ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር በፖለቲካ መቀመቅ ውስጥ ገብታ ትገኛለች፡፡ በትግራይ ፋሽስቶች በተደገሠላት የዘር ፖልቲካ ክፍፍልና ብጥብጥ ሳቢያ ወደ ለየለት የማህበረሰብ ቀውስ እየገባች ያለች አገር ነች።

"ኢትዮጵያን ለማጥፋት አማራን ማጥፋት" በሚል ስልት፣ የአማራው ነገድ በአማራነቱ ብቻ ኢላማ ተደርጎ የዘር መጥፋትና የልዩ ልዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ሰለባ እንዲሆን ሲደረግ ቆይቷል፡፡ በመሆኑም በቀጣይ ህልውናውን በተመለከተ፣ እንደ አንድ ህዝብ የመቆየቱ ጉዳይ ሲታሰብ እጅግ አሳሳቢ ወሳኝ ሁኔታና ጊዜ ውስጥ ይገኛል፡፡

የዐማራ ወጣቶች በኢትዮጵያ የተሻለ ሥርዓትን ለማምጣት የከፈሉት ውድ የሕይወት መስዋትነት በትግራይ ዘረኛ ፋሽስቶች ተክዶ፣ ቀደም ሲል በአገሪቱ ውስጥ ለተከሰቱ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች፣ ዐማራውን ብቸኛ ተጠያቂ በማድረግ፣ በጥፋተኝነት ፈርጀው ለመበቀል ሌሎችን በማስተባበር ጭምር በስፋት ዘመቱበት።

ዐማራውን ከኢትዮጵያ የፓለቲካዊ ሥልጣን ተጋሪነት፣ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ እድገት ባለድርሻነትና ተጠቃሚነት በማግለል፣ አዳከሞ ለማጥፋት ሆን ተብሎ በተሰላ መንገድ ተዘምቶበታል። ይኸውም ሌሎች በቀጥታ በአማራው ላይ የዘር ማጥራትና የዘር ማጥፋት ዘመቻ

እንዲያደርጉ በመገፋፋትና በማዘመት ያሰጭፈጨፉት ሲሆን፣ አልያም ሌሎችን እርስ በርስ እንዲጋጩ በማድረግ፣ ዐማራውን የእርስ በርስ ግጭትና የበቀል መወጫ ሰለባ እንዲሆን በማድርግ ጭምር ነው። በዚህም የዘር ማጥፋት ተግባር፣ እስካሁን ድረስ ከአምስት ሚሊዮን በላይ የዐማራ ሕዝብ ባሰቃቂ ሁኔታ እንዲያልቅ ተደርጓል።

በተለያዩ ጊዚያት በበደኖ፣ በአርባጉጉ፣ በወተር፣ በአርሲ፣ በነጌሌ፣ በአሰቦት ገዳም፣ በአሶሳ፣ በጎንደር በአደባባይ ኢየሱስ፣ በወልቃይት ጠገዴ፣ በጌዲዎ፣ በጉጂ፣ በምስራቅ ወለጋ፣ በጅጅጋ፣ በጉሙዝና በቤንቺ ማጂ ዞን፣ በወላይታ፣ በጉራ ፈርዳና በተለያዩ አካባቢዎች ዐማራውን ዒላማ ያረገ ኢሰባዊ ጭፍጨፋ ተካሂዶ ከፍተኛ እልቂት ተፈጽሟል። ይህ ጸረ አማራ ዘመቻም አዲስ አበባ ውስጥ በሚኖሩ አማሮች ላይ በረቀቀ መንገድ ሲተገበር ቆይቷል፡፡ ለምሳሌም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሰረታቸው ሆነ ተብሎ በሚሰራ ደባ ሲናጋባቸው ቆይቷል፡፡ ያለማቋረጥ በቀጠለው ግፍ በሁሉም አቅጣጫ ዐማራው ተከላካይ እንዳይኖረው በማፈን ከአገሪቱ የተለያዩ ከፍሎች እያፈናቀሉ ከዐማራ የጸዳ አካባቢ እየፈጠሩ ይገኛሉ።

በተጨማሪም ከጎንደር፣ ከጎጃም፣ ከወሎና ከሸዋ ለም መሬቶቹ ከዐማራው ተነጥቀው፤ ለሌሎች በቋንቋ ለደለደሏቸውና ለጊዜው ለሚፈቅዷቸው የአገሪቱ ጎሳዎች ታድለዋል። ከዚህ ውስጥ የአንበሳው ድርሻ ወደ ትግራይ ተከልሏል። አልፎ ተርፎም ለጎርቤት አገር ሱዳን ከፍተኛ የቆዳ ስፋት ያለው የዐማራ መሬት ቆርሶ ለመስጠት ዝግጅቱ ተጠናቋል። የሱዳን ሰራዊት እና ገበሬዎች በየጊዜው ወደ አማራው ምድር መሀል በማናለብኝነት ዘልቀው በመግባት አማራውን እየገደሉ ከብቱንና ንብረቱን እየዘረፉና እያቃጠሉ እንዲፈነጩ በር ከፍቶላቸዋል።

ህወሀትና መሰሎቹ ወደፊት ትናንሽና የተበጣጠሰች ሃገር እንድትሆን ለሚቋምጡላት ኢትዮጵያ፣ “የጎጥ መንግስታት“ የመመሥረት ህልማቸውን በማስፈጸም ረገድ፤ ዐማራውን አስጊ እንቅፋት ሃይል አድርገው በመውሰዳቸው፣ ማብቂያ በሌለው የጎሳ ጦርነት ውስጥ ሊዘፍቁት ከወዲሁ የዘረኝነት ፓሊሲ ነድፈው ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

የዐማራን ሕዝብ ቆጠራ ውጤት በማዛባት፣ ከዐማራ የፀዳ ቢሮክራሲ፣ ከዐማራ የፀዱ ከተሞችና ከዐማራ የፀዱ አካባቢዎች በመፍጠር፣ በአማራው ላይ በሁለንተናዊ መልኩና በተቀነባበረ ተንኮል ተጽእኖ እያረጉበት እና እያዳከሙት ይገኛሉ፡፡ ላለፉት 25 ዓመታት አማራው ከሥራው ሲባረር፤ ከእድገት ሲታገድ፤ የንግድ እንቅስቃሴው በአሻጥር ሲገታ፤ ያፈራው ሀብትና ንብረት ሲመዘበርና ሲዘረፍ፤ ከትውልድ ቀየውና ካገሩ፣ ከርስቱና ከጎጆው ሲፈናቀል፣ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያለ አንዳች ጥፋት በማንነቱ ብቻ ሲባረር፣ በየትኛውም የሃገሪቱ ክፍል ሠርቶ የመኖር መብቱ ሲገፈፍ፣ ታሪካዊ ማንነቱ ሲጎድፍና መሳለቂያ ሲደረግ ቆይቷል።

የአገሪቱ የፖለቲካ፤ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ስሪቶች ሙሉ በሙሉ ዐማራውን በማግለል የተቀየሱና አማራውን ከተሳትፎና ተጠቃሚነት እንዲያቅቡ ሆን ተብለው የተቀየሱ ናቸው። በዚህም ፀረ ዐማራ ተልእኮ አማራው ይበልጥ እንዲደኸይና የበይ ተመልካች አጋፋሪ እንዲሆን የሚያደርግ ስልታዊ እቅድ ነድፈው ሲሰሩበት ቆይተዋል።

የእምነት ተቋማት ከአማራ ጋር እንደባላንጣ ተፈርጀው፣ በአገዛዙ ጣልቃ ገብነት መንፈሳዊነታቸው ቀርቶ ፖለቲካዊ መድረኮች እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡ ዘመናትን ያለፉ እድሜ ጠገብ የአማራው አንጡራ ንዋየ ቅዱሳትና መዛግብት ተመዝብረው ተሸጠዋል፡፡ በአጠቃላይ በአማራው ሀይማኖታዊ እና ባህላዊ ውርስና ቅርስ ላይ ይሄ ነው ተብሎ ሊነገር የማይችል መጠነ ሰፊ ዘመቻ ሲካሄድበት ቆይቷል፡፡

ባጠቃላይ የትግሬ ሕዝብ ነፃ አውጭ ግንባር ፋሽስታዊ አገዛዝ፣ ለኢትዮጵያ እድገትና ሠላም ብሎም ለሕዝቧም ብሔራዊ ጥቅም የቆመ አይደለም። እንደውም ከሃገሪቱ ታሪካዊ ጠላቶች ጋር

በማበር፣ ቀደም ሲል ቅኝ ገዝዎች ይከተሉት የነበረውን የመከፋፈል አጀንዳ ለማስፈጸም ታጥቆና ተደራጅቶ የመጣ፣ ይበልጥ ህዝባዊ አንድነቷን በማናጋት፣ በኢኮኖሚዋ የተዳከመችና የተከፋፈለች ሃገር እንድትሆን የማድረግ ተልኮ የተቀበለ፣ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ሰውር እጅ ነው።

በመሆኑም በኢትዮጵያ ላይ ጎጠኝነትን በማንገስ፣ በሕዝቡ መካከል ጥላቻና አለመተማመንን በማስፈን፤ ሃገሪቱን ከምንጊዜውም በላይ በፖለቲካም ሆነ በኢኮኖሚው ረገድ የውጭ ኃይሎች ጥገኛ እንድትሆን በማድረግ እየገዛ ይገኛል። ሥርዓቱ ከውጭ በገፍ በሚያገኘው ያልተቋረጠ ድጋፍ፣ የአገዛዙን እድሜ ለማራዘም እየተጠቀመበት ያለ ሲሆን፣ ለታማኝነቱ ከውጭ መንግሥታት በሚያገኘው ምንዳና ከሃገር ውስጥ በሚዘርፈው የህዝብ ሐብት እየታገዘ፣ በአማራው አጽምና ርስት ላይ የታላቂቱን ትግራይ መንግሥት ለመመሥረት ያለውን ህልም እውን ለማድረግ ደፋ ቀና በማለት ላይ ነው።

በዚህ ህወሀት ባነሳቆላት እና ተስፋቢስ ባደረጋት ኢትዮጵያ ውስጥ የሃያ አምስት ዓመቱን የሰቆቃ ህይወት መለስ ብለን ስንቃኝ፣ ያለምንም ተከላካይና ተቆርቋሪ ባስከፊ ሁኔታ ለጥቃት ተጋልጦ የቆየው የዐማራ ሕዝብ ነው። ከሁሉም ይበልጥ የዐማራ ልጆች በኢትዮጵያ የተሻለ ሥርዓት ለማምጣት ግምባር ቀደም ሆነው ክቡር ሕይወታቸውን የሰውለት ትግል ዛሬ ተመልሶ ራሳቸውን ሲውጥ መስተዋሉ ህውሐት በዐማራው ላይ የሚከተለው የፖለቲካ ሴራ ምን ያህል ጥልቀት እንዳለው ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው።

ቀደም ብሎ በዐማራው ሕዝብ ላይ እየደረሰ የነበረውን ግፍና መከራ በመረዳት፣ በወቅቱ የተፈፀመውን ጥቃት ለማስቆምና የወደፊቱንም አስጊ ሁኔታ መልክ ለማስያዝ እንደ አደጋ ተከላካይ ፈጥነው የተገኙት ሰማዕቱ መሪያችን ክቡር ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ፣ የመላው ዐማራ ሕዝብ ድርጅት መዐሕድ መሪና ጥቂት የትግል አጋሮቻቸው ብቻ ነበሩ። በወቅቱም ሆነ እስከ አሁን ድረስ የትኛውም የፓለቲካ ድርጅት ለአማራው ሕዝብ ህልውናና ተፈጥሯዊ የመኖር መብት መከበር የቆመም ሆነ የታገለ ከቶ አልነበረም፤ የለም። በመሆኑም የዐማራ ሕዝብ ማንኛውንም ግፍና መከራ በጸጋ ተጋፍጦ የመከራ ኑሮውን እየገፋ ይገኛል።

## አማራው መደራጀት ለምን አስፈለገው ?

እስከአሁን አማራው በአማራነቱ ተደራጅቶ ራሱን ሊከላከል ያልቻለባቸው ምክንያቶች ብዙ ቢሆኑም ጥቂቶቹን ለአብነት ለመጥቀስ፡-

1) የኢትዮጵያ ምሠሦ የሆነው የዐማራ ህዝብ ተደራጅቶ ራሱን መከላከል ከጀመረ "ኢትዮጵያ ያልቅላታል" የሚለው የአፍቃሪ አንድነት ወገኖች ስጋት፣ የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ወደከፋ እቅጣጫ እየሄደ መሆኑንና በእነሱ መልካም ምኞትና ፈቃድ እንደማይገታ፣ ብዙዎች አስቀድመው እንዳይረዱ ስላዘናጋቸው፤
2) አማራ በታሪካዊ እድገቱና አመጣጡ እንዲሁም በሚከተለው እምነትና ማህበራዊ ፍልስፍና የተነሳ፣ ጠባብ አስተሳሰብንና የጎሳን አመለካከት ገና ማለዳ ጥሎት የመጣ በመሆኑ፣ አሁን የተላበሰው ሰብዕና ከጎሳው ይልቅ ብሔራዊ (አገራዊ) አንድነትን፣ ሉዓላዊነትን፣ ብሔራዊ ክብርንና በእኩልነት አብሮ ማደግንና ተቻችሎ መኖርን በማስቀደም ላይ የተቃኘ በመሆኑ፤

3) አማራው ጠባብ የዘር አመለካከት ስለሌለውና ከሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች ጋር በእምነት፣ በባህል፣ በስነ-ልቦና፣ በኢኮኖሚና በመልክዓ-ምድር ተላምዶ ለአያሌ ዘመናት በሠላም የኖረ ህብረተሰብ በመሆኑ፤

4) ብዙዎች ለአማራ "በኢትዮጵያዊነት ጥላ ከመሰባሰብ ውጭ ሌላ አማራጭ የለውም፣ አማራነት ብሎ መቆም አያምርበትም፤ ይህ ዘረኝነት ነው" የሚል የአመለካከት ድንዛዜና አዚም የያዛቸው፣ አማራው በራሱ ጉዳይ ታዛቢ ሆኖ እንዲቀመጥና በፍረሐት ድባብ እንዲዋጥ አሉታዊ ሚና በመጫወታቸው ጭምር ነው።

በዚህም ምክንያት፣ በተለይም የዐማራው ተወላጅ ምሁራንና አባት ሽማግሌዎች ከፍተኛ የሆነ ድንዛዜ ውስጥ ወድቀው በመቆየታቸው እና የተንቀሳቀሱትም ቢሆኑ የአማራውን ህልውና አደጋ ውስጥ መውደቁን በውል መገንዘብ ያልቻሉ ስለነበሩ፣ አማራውም ሆነ ሃገሪቱ መመለስ ወደ ማይችሉበት የፖልቲካ ማጥ ውስጥ ለማስገባት ለትግራይ ወያኔ መልካም አጋጣሚ ፈጥሮለታል።

ይሁን እንጅ፣ የአማራው ስነልቦና ከራሱ አልፎ በኢትዮጵያዊነት አውድ ዙሪያ መገንባቱ አማራነቱን ከጎጠኞቹና ከታሪክ ጠላቶቹ አዕምሮ ውስጥ ሊፍቀው አልቻለም። በሌላ በኩል ሲታይ፣ አማራነቱን ረስቶት፣ ወይንም ሌሎች እንደሚመኙት ጠልቶትና ንቆት እንዳልሆነ በሁሉም ዘንድ (በጠላትም በወዳጅም) ዘንድ ግልጽ ማድረግ የግድ ብሏል።

ከእንግዲህ በአማራው ህይወት ላይ የሚካሄደው ግፍና ሰቆቃ እልባት ሊደረግለት ይገባል። በሕዝቡ ላይ የሚደርሰው ግፍና በደል የሰው ልጅ ሊሸከመው ወይም ሊታገሰው ከሚችለው በላይ አልፏል። የግልና የወል ነጻነቱ ከመገፈፉ፤ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መሰረቱ ከመናጋቱ፤ ፖለቲካዊ ተሳትፎው ከመታገዱ አልፎ እንደ ህዝብ የመኖር ህልውናው ከባድ ጥያቄ ውስጥ ወድቋል። ስለሆነም፣ የዐማራ ልጆች የሆኑና ለህሊናቸው ያደሩ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ለአማራ ህልውናና የዜግነት ሙሉ ሙብት መረጋገጥ ያለምንም ማወላወል ሊታገሉ ይገባል።

ዳግማዊ መዐሕድ፣ የአማራ ህዝብ ህልውና የሚከበረው፣ ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቹ፣ ብሔራዊ ክብሩና ታሪካዊ ማንነቱ የሚረጋገጡት፣ ጠንካራ ብሄረተኛ አቋም ሲያራምድና ይኸው

አቋሙ በራሱ ጠንካራ የፖለቲካዊ ድርጅት እየተመራ፣ ሁለገብ ብሄራዊ ትግል በማድረግ እንደሆነ አበክሮ ያሰምርበታል፡፡

ስለሆነም፣ ሁሉንም አማራ በአንድ ጥላ ስር ሊያሰባስብ የሚችል አንድ ጠንካራ የፖለቲካዊ ተቋም መገንባት እጅግ አስፈላጊና ቀዳሚው የአማራ ልጆች ተግባር ነው። የዳግማዊ መዐሕድ መመሥረትም ይህንኑ ታላቅና የተቀደሰ ህዝባዊ ዓላማ ከግብ ለማድረስ ነው።

ዳግማዊ መዐሕድ፣ የአማራ ብሔርተኝነት ቀደም ሲል በአባቶች የተገነባ የመንፈስ አንድነትና ጥንካሬ፣ የሃገር ፍቅር፣ የነጻነት ወዳድነትና በሔራዊ ክብር እሴቶች ላይ የተመሠረተ እንደሆነ ያምናል። ይህንንም በጠንካራ ባህላዊ፤ ስነልቡናዊ፤ ታሪካዊ፤ ስነጽሁፋዊ እና ስነጥበባዊ አሻራዎች በመታገዝ ያዳብራል፡፡ በሂደቱም እንደ አንድ ሰው

አሳቢ፤ አንድ አንድ ልብ መካሪ፣ እንደ አንድ ሠራዊት ተማሚ የሚሆንበት አንድ የወል የፖለቲካ ፓርቲ እንዲመሠረትና ሁሉም አማራ በነፃነት እንዲሳተፍ ያደርጋል፡፡

ስለሆነም ይህንን ታላቅ አማራዊ ተልእኮ በአስተማማኝ ሁኔታ ዕውን ለማድረግ፤ የአማራው ህዝብ መደራጀት አስፈላጊና ወሳኝ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ለመደራጀቱ ዋና ዋና ምክንያቶቹ ከሆኑት መሐል ለአብነት፡-

ሀ. በአማራው ህዝብ ላይ ላለፉት ሠላሣ ሥድሥት ዓመታት በረቀቀ መንገድ አካላዊ፣ስነልቦናዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቃት ተፈጽሞበታል። ዛሬም ከመቸውም ጊዜ በከፋ ሁኔታ ይበልጥ በተጠናከረና በተቀነባበረ መልኩ መጠነ ሠፊ ጥቃት እየተፈጸመበት ይገኛል። ከ5 ሚሊዮን በላይ አማሮች በግፍ ከምድረ-ገጽ እንዲጠፉ መደረጋቸው አልበቃ ብሎ፣ ሰብአዊና የዜግነት መብታቸው ተገፎ፣ እንደሰው በማይቆጠሩበት ደረጃ፣ በአማራነታቸው ብቻ ከመኖርያ ቀያቸውና ሃገር እንዲፈናቀሉ በማድረግ፣ ባሰቃቂ ሁኔታ በግፍ በመግደል፣ በማሰርና በመደብደብ፣ ጥረውና ግረው ያፈሩትን ሐብት ንብረት በማናለብኝነት በመዝረፍ ይህ ነው የማይባል ግፍና በደል የተፈጸመባቸውና እየተፈጸመባቸው ያለ በመሆኑ፣

ለ. ከዐማራ የጸዳች ሃገር ለመፍጠር ሕውሐት አልሞና አቅዶ በተነሳው መሠረትና በተግባር ባደረገው ፀረ-አማራ ዘመቻ፣ ከአማራ የጸዱ የመንግስት ተቋማት፣ ከተሞችና አካባቢዎች እየተፈጠሩ በመሆናቸው፣ በተለይም በጎንደርና በወሎ በታሪክ የዐማራው መኖርያና ጥንተ-ይዞታ የነበሩ አካባቢዎች በሃይል ተገደው በቅኝ ግዛትነት እንዲተዳደሩ በመደረጉና ነዋሪውም ሕዝብ በግድ “ትግሬ ሁን” እየተባለ፣ ልዩ ልዩ ጫናና የግፍ እርምጃ እየተወሰደበት ማንነቱን እንዲቀይር በመደረጉና እየተደረገ በመሆኑ፤

ሐ. የአማራ ሕዝብ በመላ አገሪቱ የፖለቲካም ይሁን የኢኮኖሚ ልማት ባለድርሻና ተጠቃሚ እንዳይሆን በመደረጉ፤ የዜግነት መብቱ ተገፎ፣ ህልውናውና ታሪካዊ ማንነቱ ተክዶ፣ ሃገራዊም ስሜትም ይሁን ማህበራዊ ዋስትና እንዲያጣ በመደረጉ እና ይኸው የጥፋት ተግባር ይበልጥ ተጠናክሮ የቀጠለ በመሆኑ፤

መ. አማራው ሃይማኖቱ ሳይቀር በሌላው ህብረተሰብ ዘንድ እንዲጠላና ተቀባይነት እንዲያጣ በመደረጉ፣ ታሪኩ በአውሬነት እየተመሰለ የቀደሙት ነገሥታትና መሪዎችን እንደበደለኛ በመቁጠር ሰርተውታል ብለው ለሚያስቧቸው ጥፋቶች ብቸኛ ተጠያቂ ተደርጎ እንዲታይና እንዲገለል በመደረጉ፣ ከዛም አልፎ እንደ ጠላት ተፈርጆ ሁሉም ባገኘበት እንዲያሳድደው በመርሀ ደገኛ አቋም ተይዞ በወያኔ ዘርኞችና መሰሎቻቸው እየተሠራበት ያለ ጉዳይ በመሆኑ፤

ሠ. ኢትዮጵያን ለማጥፋት አማራን አስቀድሞ ማጥፋት የሚለው የዘረኛውና አምባገነኑ ህወሀት አማራን ከምድረ ኢትዮጵያ ለማጥፋት የረቀቀና የተቀነባበረ ፕሮግራም ነድፎ በመንቀሳቀሱ፤ የአማራን ትውልድ ተከታታይና ቀጣይ ጉዞ ለመግታት ሲባል የአማራን ሴቶች እስከማምከን፣ በቀሳፊ በሽታ እንዲያዙ እስከማድረግ የደረሰ እጅግ ዘግናኝና አስከፊ ኢ-

ሰብአዊ ተግባር እየፈጸሙበት ያለና በቋሙ እልቂት የተፈረደበት ህዝብ በመሆኑ፤

ረ. የዐማራን ሕዝብ ስቃይና ሰቆቃ ቅድሚያ ሰጥቶ በባለቤትነት ታግሎ ሊያታግል የሚችል የቆረጠ ድርጅት እስካሁን ባለመፈጠሩ፣ ቢኖሩም ከየድርጅቶች የፖለቲካ ፍጆታ ያለፈ ተግባርና ትኩረት ባለማድረጋቸው፣ በዚህም ምክንያት አማራውም ላይ ሆነ በአገራዊ ደረጃ በተከሰተው የፖለቲካና ማህበራዊ ቀውስ ዐማራው ራሱን በስፋት ከተቃጣበት ጥቃት ተከላክሎ የኃይል ሚዛን የሚያስጠበቅ ወሳኝ ሚና ለመጫወት ይበቃ ዘንድ፤

ሸ. ምናልባት የኢትዮጵያ ፖለቲካ እንደሚፈራው እልባት አጥቶ፣ አገሪቱ የመበታተን እጣ ቢገጥማት፣ ለአማራው ሙሉ ታሪካዊ መብቱንና ድርሻውን በባለቤትነት ታግሎ የሚስረክብ ድርጅት የግድ በማስፈለጉ፤ በብሄረሰቦች መካከል እያደገ የመጣውን ቅራኔና ስጋት አጢኖ በአማራው ላይ ሊደርስ የሚችለውን የዘር እልቂት ለመከላከል አስቀድሞ መዘጋጅት አስፈላጊ በመሆኑ፣ ለዚህም የዐማራውን ስነልቦና መገንባት፣ አካላዊ ደህንነት መጠበቅ፣ ፖለቲካዊ ንቃቱን ማጎልበት ወዘተ እጅግ ወሳኝና በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

በአጠቃላይ በግፍ የፈሰሰው የዐማራ ሕዝብ ደም፣ የዐማራ ሕዝብ ሰቆቃና ብሶት፣ እንዲሁም አማራው ላይ የተደቀነው መጭው አደጋ አማራን ታዳጊ ወይም ነፍስ አድን የፖለቲካ ድርጅት ወልዷል። ይሄውም "ዳግማዊ የመላው ዐማራ ሕዝብ ድርጅት" (ዳግማዊ መዐሕድ) ነው።

በዳግማዊ መዐሕድ እምነት ኢትዮጵያ ለሁሉም የጋራ አገር ናት። ለኢትዮጵያ እድገትም ሆነ ውድቀት፣ ሃላፊነቱም ሆነ ተጠያቂነቱ የጋራ ነው። የዐማራ ሕዝብ በተናጠልም ሆነ በጋራ ለብቻው የሚያስጠይቀው ምንም አይነት ነገር አይኖርም። ስለ አገር መቆርቆር ሰዎች በግልና በጋራ የሚወጡት ብሔራዊ ግዴታ ነው። በዚህም ዘይቤ ዳግማዊ መዐሕድ የአማራ ህልውና ተረጋግጦ ሁለንተናዊ ችግሮች እስከተቀረፉ እና እንዲሁም የተጋረጠበት የዘር እልቂት እስከተገታ ድረስ፤ የኢትዮጵያ ጉዳይ በሁሉም ዘንድ በጋራ እንደ ጋራ ጉዳይ ተቀባይነት አግኝቶ ለአማራ በተለየ ሸክምነት መሰጠቱ እስከቆመ ድረስ በኢትዮጵያ ሉአላዊነት ላይ ጥያቄ የለውም፡፡ ለአማራ ክብር የምትሰጥ አገር፤ አማራ እንደወርድና ቁመቱ ድርሻውንና ጥቅሙን የሚያስከብርባት አገር እስከሆነች ድረስ፣ ኢትዮጵያን በጋራ ለመገንባት በሚደረገው ማናቸውም ጥረት ከመሳተፍ ወደኋላ አይልም፡፡ አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ ለተከሰቱት ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፤ ፖለቲካዊና ብሄረሰባዊ ቅራኔዎች በቅንነትና በታማኝነት መፍትሄ ለማምጣት ከሚጥሩ አካላት ጋር በጋራ ሆኖ የመፍትሄ አካል ለመሆን የሚሰራ መሆኑን አበክሮ ያረጋግጣል፡፡ ነገር ግን ይህ ሳይሆን ቀርቶ የኢትዮጵያ ሁኔታ ከቁጥጥር ወጥቶ፣ ባልተፈለገው አቅጣጫ የሚሄድ ከሆነ፤ ዳግማዊ መዐሕድ ዐማራው በሔራዊ ደህንነቱን፣ ሠላሙን፣ ሙሉ መብቱንና ሃገሩን የሚያስከብርበትንና የሚያረጋግጥበትን እድል ለመፍጠር ተግቶ ይሠራል፡፡

ዳግማዊ መዐሕድ የሕዝብ አንድነትና ፍቅር፣ ቀና አመለካከትና መቻቻል የሁሉም የጋራ ፍላጎትና የድርጊት ውጤት ነው ብሎ ያምናል። በኢትዮጵያ አገራዊ አንድነትና ፍቅር እያመካኙ ዐማራውን በየዘመኑ ለሚነሱ ጽንፈኞች የፖለቲካ ፍጆታ የማዋሉ ተግባር መገታት አለበት ብሎ በጽኑ ያምናል። በዚህም ሰነድ፣ ዳግማዊ መዐሕድ ለዐማራ ሕዝብ ደህንነት፣ ሰላምና ዕድገት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ የሚታገልና የሚሠራ የፖለቲካ ድርጅት መሆኑን በግልጽ ያሳውቃል።

## 1. ራዕይ:-

ዳግማዊ የመላው ዐማራ ሕዝብ ድርጅት (ዳግማዊ መዐሕድ) እውን እንዲሆን የሚሻው:-

**ሀ.** የዐማራ ሕዝብ በትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጭ ግንባርና ተባባሪ ጎጠኞች፣ እንዲሁም በታሪክ ጠላቶቹ ድጋፍ የተቃጣበትን የተቀነባበረ ጥቃት በማከሸፍ፤ ዐማራው በአገሩ የተነፈገውን የዜግነትና የባለቤትነት መብት መልሶ በማረጋገጥ፣ በአገሩ ኢትዮጵያ ውስጥ በፈቀደው ቦታ ሰርቶ የመኖር መብቱን ማስከበር፤

ለ. የዐማራ ሕዝብ በጎጠኛው የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጭ ግንባር ፋሽስታዊ አገዛዝ የሚፈፀምበትን ጥቃትና በደል፣ እስራትና ግድያ፣ ንብረት ዘረፋና ዘርፈ- ብዙ እንግዳ አስወግዶ፣ ነፃ የሆነ የሕግ የበላይነት የተረጋገጠበት፣ የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተከበረበት፣ ኃላፊነትና ተጠያቂነት ያለበት፣ እንዲሁም የአገሪቱ አመራር በግልጽነት፣ በአኩለነት፣ ከሕዝብ የሚመነጭና ለሕዝብ ፍላጎት የሚገዛ ሥርዓት በመፍጠር፣ ለምጣኔ ሃብት፣ ለፖለቲካና ለሕዝብ ዕድገት ተባብሮ የሚሰራ ሕብረተሰብ ማየት፤

**ሐ.** የአማራን ህዝብ ክብር፤ ነጻነት፤ ልዕልናና ብልጽግና ማረጋገጥ ቀዳሚ ተግባሩ ከመሆኑ አንጻር በኢትዮጵያ ህዝብ ሉዓላዊ አንድነት ላይ እያንዣበበ ያለው አደጋ አዝማሚያው የከፋ የሚሆን ከሆነ ለአማራው ህዝብ የተሻለውን የመፍትሄ አቅጣጫ በመቀየስና አስፈላጊውን እርምጃ ሁሉ ፈጥኖ ወስዶ ሁለንተናዊ ህልውናውና ደህንነቱ ተረጋግጦ ማየት ናቸው፡፡

## 2. ዓላማ

**ዳግማዊ መዐሕድ ዓላማው:-**

ሀ) የአማራ ህዝብ፣ ታሪኩ በትግራይ አምባገነን ዘረኞችና ሌሎች መሰል ጠባብ ጎጠኛ ቡድኖች በገሃድ ተከዶ፣ በሃገሪቱ የነበረው እየወደመ፣ ያልነበረው እንደነበረ እየተቆጠረ፣ በሃሰት በተፈበረከ ስንክሳር ተወቃሽና ተከሳሽ እንዲሆን የተደረገበትን ደባና፣ በአባቶቹ፣ በአያቶቹና ቅደመአያቶቹ አጥንት በተገነባች ሃገሩ፣ የተጋሪነት መብቱን ተነፍጎ፣ ባልሠራው ነገር የታሪክ ተወቃሽ እንዲሆንና በሁሉም ሀበረተሰብ ዘንድ በጠላትነት ተፈርጆ እንዲታይና እንዲገለል ብሎም በበታችነት ተዋርዶና ተሳቀሎ እንዲኖር፣ የሌሎች ተገዥ እንዲሆን ለማድረግ እየተሠራ ያለውን ብሔራዊ በደልና የግፍ ጭቆና መታገልና ማስቆም፤

ለ) አማራው ለታሪኩ፣ ለብሔራዊ ደሕንነቱና ሉዓላዊነቱ መከበር በቁርጠኝነትና በፅናት እንደሚታገል ማረጋገጥ፣ ሰንደቅ ዓላማውም ከራሱ አልፎ ለመላው ጥቁር ዘርና ጭቁን ሕዝብ የነጻነት ጎህ ፈንጣቂና የብሩህ ተስፋ ምልክት የሆነው፣ በአረንጓዴ፣

ቢጫና ቀይ ሕብረ ቀለም ያሸበረቀችው የጥንቱ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ሆኖ በክብርና በኩራት እያውለበለበ፣ ህልውናውን ማስከበር እና የአማራው ትግል ከራሱ ህልውና እና መብት መከበር አልፎ ለተቀሩት ጭቁን ኢትዮጵያውያን ሁሉ ብርቱ የነፃነት አጋር ሆኖ እንዲቆም ማስቻል፤

ሐ) የዐማራውን ሕዝብ የብሔር አንድነትና ደህንነት ማስጠበቅ፣ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቱ እንዲረጋገጥ ማድረግ፤ ፖለቲካዊ፣ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞቹን ማስከበር፣ እንዲሁም፣ አባቶቹ በመሠረቱት የወንድማማችነት፣ መፈቃቀድና እኩልነት መንፈስ በብዝሐ-አንድነት ላይ የተመሠረች ኢትዮጵያ ታፍራና ተከብራ፣ ጽንታ እንድትኖር፣ የጋራ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እሴቶቻችንና ጥቅሞቻችን በጋራ እንዲከበሩ፣ የሃገርን ሉዓላዊነትን ቁርጠኝነት ካላቸው ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር በአንድነት ለማስከበር ይታገላል፡፡

መ) በዐማራው ህዝብ ላይ እየተፈጸመ ያለውን የዘር ማጥፋትና የዘር ማፍለስ አረመኔያዊ ተግባር በማስቆምረገድ፤ ዐማራው በአገር ውስጥና ከሃገር ወጭ ተደራጅቶ ራሱን ከጥቃት ሊከላከል የሚችልበትን ሁለንተናዊ አቅምና ብቃት መፍጠር፤

ሠ) የአማራ ትግል ተገቢ ዓለማቀፋዊ ተቀባይነት እንዲኖረውና በብቃት እንዲደገፍ፣ እንዲሁም አግባብ ካላቸው ዓለማቀፍና መንግሥታዊ ተቋማትና ድርጅቶች ጋር የዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት መመሥረት፣ የዐማራ ትግል ደጋፊና አጋዥ የሚሆኑ ሃይላትንና ግለሰቦችን ማሰተባበር፣ ማንኛውንም ፀረ-አማራ ተግባራት መቃወም፣ ማውገዝና ለዓለማቀፉ ህብረተሰብ እየተከታተሉ በየጊዜው ማጋለጥ እና፤

ረ) የዐማራ ሕዝብ የራሱ ትክክለኛ የመረጃ ስርጭት በአስተማማኝ ሁኔታ እንዲኖር ማስቻልና

የተሟላ የማህበራዊ መረጃ አውታርና የብዙሃን መገናኛ ማእከል ባለቤት ማድረግ የዳግማዊ መዐሕድ ተቀዳሚ ዓላማዎቹ ናቸው።

**ዳግማዊ መዐሕድ የሚከተላቸው መሠረታዊ መርሆዎችና ዕሴቶች:-**

**ሀ. የግለሰብ ነፃት :-**

የሰብዓዊና የዲሞክራሲያዊ መብቶችን ያከብራል። ዜጎች ቋንቋቸውን የመጠቀምና የማሳደግ፣ ባህልን የማዳበርና እምነትን፣ ልማድን፣ ሰነስርዓትን ተግባራዊ የማድረግ መብት አላቸው። የቡድን እና የጋራ መብቶችን እንደ የሴቶች፣ የወጣቶች፣ የሙያ ማሕበራትና የመሳሰሉ የስብስብ መብቶችን ያከብራል።

**ለ. ግንኙነቶች:-**

ዳግማዊ መዐሕድ በግለሰቦች መካከል፣ በቡድኖች መካከል፣ በግለሰብና በቡድኖች መካከል ያሉ ግንኙነቶች ተነቃናቂና ተለዋዋጭነታቸውን በመገንዘብ ሚዛናዊና እድገትን አመላካች እንዲሆኑ፣ መብት ከሃላፊነት ጋር መተሳሰር እንዳለበት ያምናል። ታማኝነት፣ ሃቀኝነት፣ ትክክለኝነት፣ ግልጸኝነት፣ ተጠያቂነት፣ ምላሽ ሰጭነት፣ ተቆርቋሪነት፣ መልካም አርአያነት የመሳሰሉ ኃላፊነቶችን መብት ከማስከበር ጋር ትስስርነት እንዳላቸው ይገነዘባል። በተግባር ላይ እንዲውሉም ያለማቋረጥ ጥረት ያደርጋል።

**ሐ. አንድነት በልዩነት:-**

ቋንቋ፤ ሃይማኖትና ባህል የማንኛውም ህብረተሰብ የማንነቱ መገለጫ በመሆኑ፣ ዳግማዊ መዐሕድ እነዚህንና መሰል የማንነት መገለጫዎች ህብረተሰቡ እንዲያሳድግ እና እንዲጠቀም ይታገላል፡፡ አንዱ በሌላው ላይ ተጽዕኖና አድልዎ እንዳያደርግ ይታገላል። ሕብረተሰቡም ጥብቅ በሆነ የአንድነት መሠረት ላይ እንዲቆም ያልተቆጠበ ጥረት ያደርጋል።

**መ. ዴሞክራሲ:-**

የብዙሃን መንፈስ የተንፀባረቀበት የአስተዳደር ሥርዓት ከሕዝብ፣ በሕዝብ ለሕዝብ የተመረጠ እንደመሆኑ መጠን፣ ማንኛውም ሰው ራሱን በሚነካ ውስኔ ላይ ሃሳብ የመስጠት መበት እንዳለው ዳግማዊ መዐሕድ ያምናል። ግለሰቡ የመምረጥም ሆነ የመመረጥ፣ ሃሣብ የመስጠትና የመተቸት (በመንግስት፣ በሥራ ቦታ፣ በአካባቢና፣ በብሔራዊ ደረጃ) መብቱ የተከበረ መሆኑን አጽንኦት ሰጥቶ ይታገላል፡፡

**ሠ. አሳታፊነት፣ አሰባሳቢነት:-**

ዳግማዊ መዐሕድ ሕዝቡ በፖለቲካ፣ በምጣኔ ሀብት፣ በማሕበራዊ፣ በዴሞክራሲና በሰብዓዊ ግንዛቤዎች፣ በባለቤትነት መንፈስ ሙሉ ተሳትፎ ያለው ዋነኛ ኃይል መሆን አለበት ብሎ ያምናል።

**ረ. የጋራ ጥቅም :-**

ዳግማዊ መዐሕድ ባንድነት መንፈስ ለጋራ ተጠቃሚነትና የወል እድገት ተቀናጅቶና ተግባብቶ መሥራት አስፈላጊ እንደሆነና ጠቀሜታው የላቀ እንደሆን ያምናል። ለወደፊት ለበሔራዊ ደህንነትና ህልውና ወሳኝነት እንዳለው ስለሚያምን ለተግባራዊነቱ ያልተቆጠበ ጥረት ያደርጋል።

ሰ. የትግል ስነ ስነርዓት :-

ታታሪነትና ግልፅነት ለለውጥ እንዲሁም ለዕድገት አስፈላጊ ጠባዮች ናቸው። የግለሰቦችንና የቡድኖችን ተሳትፎ ለማሳደግ፣ ገንቢ ትችቶችን ለመቀበል፣ አሳታፊና አሰባሳቢ ለሆነ ስርዓት፣ ሰላማዊ ትግል ውጤታማ ነው። ነገር ግን ከዚህ በላይ የተገለፁትን አመላካች ነጥቦች ለማይቀበል ፈላጭ ቆራጭ ለሆነ ስርዓት፤ የሕዝብ አመፅ እስከ ጠመንጃ ማንሳት ድረስ እንደሚሄድ ዳግማዊ መዐሕድ ይገነዝባል። አስፈላግነቱንም ይቀበላል።

ሸ. እኩልነት :-

ዳግማዊ መዐሕድ እያንዳንዱ ሰው ተፈጥሮዊ እኩልነት ስለአለው በጎሳ፣ በቀለም፣ በትምህርት፣ በሀብት፣ በፆታ፣ በሃይማኖት፣ በአመለካከት ወዘተ ላይ የተመሰረተ አድልዎን አይቀበለውም።

ቀ. የሕግ የበላይነት :-

ባለስልጣኖች፣ የመንግስትም ሆነ የግል፣ ሰራተኞች፣ እንዲሁም ማንኛውም ዜጋ በሕግ ፊት እኩልነታቸውን ዳግማዊ መዐሕድ ያምናል። የየትኛውም አካል ይሁን ማንኛውም ግለሰብ ለሕግ የበላይነት ተገዥ ነው።

እነዚህ እሴቶችና መርሆዎች ከጎሳ ፖለቲካ፣ ከጎጠኛ ፈላጭ ቆራጭነት ሥርዓት ነፃነት በኋላ የሚጠቅሙ ከሊብራል ዲሞክራሲና (የግለሰብ መብት፣ በውድድር ላይ የተመሰረተ የነፃ ገበያ ኤኮኖሚ) ከስምምነት ዲሞክራሲ የተጠናቀሩና ከአገራችን ሁኔታ ጋር የተቀመሩ ናቸው።

በገጠርና በከተማ በትምህርት፣ በሀብት፣ በኑሮ ሁኔታ ወዘተ ያሉ ልዩነቶችን ለማጥበብ አቅድና ጥረት ያስፈልጋል። አቅሙ ካላቸው ዜጎች የሚሰበሰበውን ታክስና ቀረጥ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ በሥራ ላይ በማዋል ኃላፊነትን መወጣት ይቻላል።

በዳግማዊ የመላው ዐማራ ሕዝብ ድርጅት እምነት የመናገር፣ የመፃፍ፣ ከቦታ ቦታ የመዘዋወር መብት፣ ነፃነት ከተጠበቀ የሕግ የበላይነት ከተከበረ፣ ሕዝቡ በመንግስት ላይ ቁጥጥር የሚያደርግበት ሥርዓት ከተዘረጋ፣ የስልጣን ክፍፍል (ሕግ አውጭ፣ ሕግ ተርጎሚ፣ ሕግ አስፈፃሚ) ሚዛናዊነቱን መቆጣጠር ከተቻለ፤ የግል ሀብት ባለቤትነትና የኤኮኖሚ ነፃነት ከተረጋገጠ፤ ውሃ፣ መብራት፣ የብዙሃን መገናኛ፣ ጤና ጥበቃ፣ ትምህርት፣ ሥራ ለሰው ልጅ አስፈላጊ ነገሮች በመሆናቸው፣ ለተጠቃሚው ዝግጁነታቸው ከተረጋገጠ፣ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች መድረስ ከተቻለ፣ የአገር ድንበርን የሚያስከብር ጠንካራ የመከላከያና ከሕዝቡ ጋር የተስማማ ሰላምና ፀጥታን የሚያስከብር የፖሊስ ኃይል ካለ፤ በችሎታውና በጥረቱ ፈጣን እድገት የሚያሳይ ከራሱ ጋር የታረቀ በአንድነቱ ኮርቶ ደስተኛ የሆነ ህብረተስብ መመስረት እንደሚቻል ዳግማዊ መዐሕድ በጥብቅ ያምናል። ይህንንም ዕውን ለማድረግ ያልተቆጠበ ጥረት ያደርጋል። በዚህ መንገድ የዐማራ ሕዝብ ህልውናውን ያረጋግጣል፡፡

## 3. የፖለቲካ መርህ :-

የዐማራን ህዝብ ሁለንተናዊ ማንነት ማስከበር፣ የሌሎች ብሔር ብሔረሰቦችን ማንነት፣ ባህል፣ እምነትና አስተሳሰብ ማክበር፣ በእኩልነት, ፍትህና መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ ሃገራዊ የሥልጣንና የሐብት ባለድርሻነትና ተጠቃሚነት እንዲኖር ማድረግ፣ የዜጎች ሰብዓዊና ዲሚሞክራሲያዊ

መብቶች እንዲከብሩና የመልከዓ-ምድራዊ አሠፋፈርን ታሳቢ ያደረገ የህዝቦች የራስን በራስ ማስተዳደር መብት እንዲከበር መታገል።

## 4. የኢኮኖሚና ልማት መርህ :-

ዐማራው ህብረተሰብ ካለበት ኋዋላ ቀርነትና ድህነት እንዲላቀቅና የኑሮ ሁኔታው እንዲሻሻል ማድረግና ለዚሁም በክልሉ ያሚገኙትን ተፈጥሯዊ፣ የሰው ሃይል፣ እውቀትና ሐብት በመጠቀም ፈጣን እድገት እንዲረጋገጥ ማስቻልና ለዚሁም ዓላማና ተግባር ውጤታማነት የክለሉን ተወላጆችና አጋር ወዳጆች በውስጥም በወጭም ሀገራት ማስተባበርና መምራት። እንዲሁም ለብሔራዊ ልማትና የጋራ እድገት ሁለገብ አስተዋጾ ማድረግ።

## 5. የማህበራዊ ጉዳይ መርህ :-

የዐማራው ህበረተሰብ መሠረታዊና ሁለንተናዊ ደህነቱ እንዲጠበቅ ማድረግ፣ በጤናማና ምቹ አካባቢ የመኖር መብቱን በማረጋገጥ፣ የጤና፣ የትምህረት፣ የምግበ፣ የንጹህ ውሀ መጠጥና የመጠለያ ፍላጎቱና አገልግሎቶች እንዲሟሉለት ማድረግ፣ በተመሳሳዩም የስልክ፣ የምንገድ፣ የመብራትና የመገናኛ በዙሃን ተጠቃሚ እንዲሆን ማስቻል።

ከማንም ተጽእኖ ነፃ በሆን መንገድ፣ ዐማራው በእኩልነት፣ ቋንቋውን፣ ሃይማኖቱንና ባህሉንና ትውፊቶቹን የማጎልበት፣ የፖለቲካ አመለካከቱን ያለተጽእኖ የማራመድ፣ እንዲሁም ተፈጥሯዊና ታሪካዊ ቅርሶቹን የመንከባከብና የመጠበቅ፣ የማስተዳደር፣ የኪነጥበብና ስነጥበብ እሴቶቹን የማሳደግ፣ ሳይንስና ቲክኒዮሎጂ ባካባቢው እንዲስፋፋ የማድረግ መብቱ እንዲጠበቅ ማስቻል።

## 6. ሰባዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች :-

እንደማንናውም ሰው ሁሉ ዐማራው በተፈጥሮው በማንም የማይገሠሥ በህይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነቱ የመከበርና የመጠበቅ ነፃነቱ እንዲረጋገጥለትና በእኩልነት የዜግነት መብቱ ተከብሮለት፣ በፈቀደው ሥፍራ ሠርቶና ሀብት አፍርቶ የመኖርም ሆነ ከቦታ ወደቦታ የመዘዋወር መብቱ እንዲጠበቅለት እና በየትኛውም የሃገሪቱ ክፍል ያለ ምንም ተጽእኖና ባይተዋርነት ፍትሐዊ የህግ ከለላ እንዲኖረው ማስቻል።

## 7. የብሔራዊ ደህነትና መከላከያ መርህ:-

### ዳግማዊ መዐሕድ የኢትዮጵያን ሕዝብ የስልጣን ባለቤት ሲያደርግ:-

የሃገሪቱ ብሔራዊ ደህንነትና የመከላከያ ሠራዊት የሁሉንም ብሔር ብሔረሰብ ተዋጾ ባግባቡ የሚያካትትና ከየትኛውም ዘርና ጎሳ ሆነ ሐይማኖት እንዲሁም የፖልቲካ ወገንተኝነት ፈጽሞ የፀዳ ሆኖ፣ በህዝብ የበላይነት የሚያምንና በህዝብ ይሁንታ ለጸደቀ የሃገሪቱ ህገ-መንግሥት ተገዢ የሆነና በህገ-መንግሥቱ መሠረት ብቻ የሚታዘዝ፣ ለህዝብ ሠላምና ደህንነት፣ ለሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብት መከበር እና ለሃገር ሉዓላዊነት ዘብ የሚቆም እንዲሆን አጽኖ ሠጥቶ ይታገላል።

## 8. የውጭ ግንኙነት መርህ:-

### ዳግማዊ መዐሕድ የኢትዮጵያን ሕዝብ የስልጣን ባለቤት ሲያደርግ:-

ሀ. ከማንኛውም የውጭ መንግሥት ተፅዕኖ ነፃ የሆነ፣ ህዝባዊ አንድነትንና ሃገራዊ ሉዓላዊነትን የሚያከብር፣ የህዝብን ብሔራዊ ጥቅም በቀዳሚነት የሚያስጠብቅ፣ በእኩልነትና በጋራ ተጠቃሚነት ላይ የሚመሠረት መርህና አሠራር ያለው የውጭ ፖሊሲ ይደግፋል።

ለ. የኢትዮጵያን የግዛት አንድነትና ብሔራዊ ጥቅምን እስካልተጋፋና የህዝቧን ጥቅም እስካልተፃረረ ድረስ፣ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የሚደረጉ ስምምነቶችንና ውሎችን ያከብራል።

ሐ. የሰው ልጅ ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን የማክበር ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎችን፣ ቻርተሮችንና ስምምነቶችን ያከብራል።

ሠ. ለዓለም ሠላምና ዲሞክራሲ ከቆሙ አገሮችና ዓለም አቀፍ ተቋሞች ጋር በመተባበር የጋራ ጥቅሞችን የሚያስከበር መርህ ይከተላል።

ረ. በሌላ አገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ባለመግባት፤ የመከባበር፣ የመተሳሰብ፣ የሰላም፣ የትብብርንና የጋራ ዕድገትን የሚያጠናክር እና ችግሮች ሲከሰቱ በሠላም የመፍታት መርህ ይደግፋል።

ሰ. በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ የውጪ ንግድ፣ የልማትና ትበበርና ግንኙነቶችን ያበረታታል።

**ሐምሌ 2008 ዓ.ም**

**ዳግማዊ መላው ዐማራ ህዝብ ድርጅት**